የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**March 13, 2025**

**Extension of Deadline for Submission of Required Documents and Information by publicly held companies as per the public notice published on February 4, 2025**

We extend our sincere appreciation to all issuers who have complied with our previous public notice by submitting the required documents and information within the stipulated period.

In consideration of requests, and to accommodate further submissions, we are extending the submission deadline by an additional **one (1) month** from the original deadline. This extension serves as a final opportunity for those who have not yet submitted their required documents to do so within the specified timeframe. We strongly urge all companies that have not yet submitted the required information to take this extension seriously and ensure submission of the necessary documents before the new deadline.

This public notice is directed at companies having more than fifty (50) shareholders (publicly held companies and companies currently raising capital through public subscription, **regardless of the sector or industry in which they operate.**

The **Public Offer and Trading of Securities Directive No. 1030/2024** ("Directive") became effective, as of **November 14, 2024**. The Ethiopian Capital Market Authority ("Authority") issued this Directive in furtherance of its objectives of ensuring investor protection and promoting an orderly, fair, efficient, and transparent capital market.

**PURPOSE OF THE NOTICE**

In light of the new Directive, this notice is primarily aimed at gathering information for regulatory purposes. The Authority requires publicly held companies to provide details on their existing shares to facilitate the integration of existing securities into the regulated capital market system.

The information gathered through this will help establish a strong information disclosure regime and ensure transparency in the market. As a result, publicly held companies are required to submit the following information to the Authority until **April 9, 2025.**

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

The company's management **must sign a statement including all documents being provided and attesting to the accuracy and completeness** of the information and documents being provided.

1. Total number of shares issued, distinguishing between total amounts of subscribed shares and total amounts of fully paid shares, and the total number of shareholders.

2. The value of the existing securities on the date they were issued.

3. For a previously completed offer or issuance, the start and end date of the offer or issuance.

4. Copies of the offer document that are used to solicit the sale of the securities. (e.g., a prospectus, notice given to shareholders regarding their preferred right of issuance, and other offer documents used by the issuer)

5. The content and media outlets of advertisements related to the offer, specifying the time of its presentation.

6. If there is an ongoing offer or issuance currently, whether for existing or new shareholders, the start and end date of this ongoing offer or issuance, details of the ongoing public offers, including shareholders resolution authorizing the issuance and other supporting documents related to the issuance.

**SUBMISSION PROCEDURE**

Hard copies should be delivered to the Authority's head office at **Minaye Building, 17th**

**Floor, Flamingo Area, Kirkos, Addis Ababa**. In addition, Soft copies should be emailed to: lgizachew@ecma.gov.et and smohammed@ecma.gov.et in **PDF, Word or Excel** format**.**

**IMPORTANT INFORMATION**

Public companies that fail to submit the required data by the specified deadline will have any share issuance considered as if it took place after November 14, 2024.

**DISCLAIMER**

**Existing Securities:** ***The submission of data based on this notice shall not constitute registration of existing securities with the Authority***. Publicly held companies must follow the registration requirements of the Directive and register their existing securities within a year, starting from **November 14, 2024**.

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**On-going offer:** Additionally, the Directive mandates that all publicly held companies conducting offers of securities initiated before the effective date of the **Directive must finalize the registration of their existing shares within a year**, starting from **November 14, 2024**.

**New offer:** Please be aware that **every security must be registered with the Authority before any offer or sale of securities**. Companies that want to make a new offer must register their securities beforehand based on the rules and procedures of the Directive.

Failure to meet these registration requirements will result in penalties as outlined in the Proclamation and the Directive.

We urge all companies concerned to comply promptly with these requirements to ensure a smooth transition to a fully regulated capital market.

**Ethiopian Capital Market Authority**

**March 13, 2025**

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**መጋቢት 4 ቀን 2017 ዓ.ም.**

**ጥር 4 ቀን 2017 ዓ.ም. በወጣው ይፋዊ መግለጫ መሰረት በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች አስፈላጊ ሰነዶችን እና መረጃዎችን የሚያቀርቡበትን ቀነ-ገደብ ስለማራዘም**

ቀደም ሲል በተላለፈው ይፋዊ መግለጫ መሰረት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ ሰነዶችን እና መረጃዎችን ላስገባችሁ ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ሆኖም የቀረቡ ጥያቄዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት እና ተጨማሪ መረጃዎችን ለመቀበል ይቻል ዘንድ የማስረከቢያ ጊዜውን አስቀድሞ ከተገለጸው የመጨረሻ የማስረከቢያ ቀን ጀምሮ **ለአንድ (1) ወር** ተጨማሪ ጊዜ ማራዘም አስፈልጓል። ይህ ማራዘሚያ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስፈላጊ ሰነዶችን ላላቀረቡ እንደ መጨረሻ እድል ሆኖ ያገለግላል። አስፈላጊውን መረጃ እስካሁን ያላቀረቡ ኩባንያዎች ይህንን ማራዘሚያ በመጠቀም የተጠየቁ መረጃዎችንን እና አስፈላጊ ሰነዶችን ከተራዘመው የጊዜ ገደብ በፊት እንዲያቀርቡ በጥብቅ እናሳስባለን።

ይህ ይፋዊ መግለጫ **ኩባንያዎቹ በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ እና ኢንዱስትሪ ሳይገደብ ከአምሳ (50) በላይ የአክስዮን ባለቤቶች ያሏቸው (በህዝብ ባለቤትነት የተያዙ)** እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ አክስዮኖችን ለህዝብ ሽያጭ በማቅረብ ከህዝብ ገንዘብን የሚሰበስቡ ኩባንያዎችን ይመለከታል።

**ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2024** (“መመሪያ”) **ከህዳር 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ** ስራ ላይ መዋሉ ይታወሳል። የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን (“ባለስልጣን”) ለኢንቨስተር ከለላ የመስጠት እንዲሁም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማውጣት እና የግብይት ስራ ስርዓትን የተከተለ፣ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ግልጽነት በሰፈነበት ሁኔታ የሚካሄድበትን የተሟላ የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳርን ለመፍጠር የተነሳበትን አላማ ከግብ ለማድረስ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብ እና ሽያጭን የሚቆጣጠር የህግ ማዕቀፍ አዘጋጅቷል።

**የይፋዊ መግለጫው አላማ**

መመሪያው ከሚያስተዋውቀው አዲስ የቁጥጥር ስርዓት ጋር ተያይዞ ይህ ይፋዊ መግለጫ ለቁጥጥር ሂደቱ የሚረዱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያለመ ነው። በዚህም መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች ነባር አክስዮኖቻቸውን ቁጥጥር ወደ የሚደረግበት የካፒታል ገበያ ለማምጣት ስለአክስዮኖቹ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያቀርቡ እንጠይቃለን።

በዚህ መልኩ የሚሰበሰበው መረጃም በገበያው ውስጥ ጠንካራ መረጃ ይፋ የሚደረግበት እና ግልጽነት የተሞላበት የገበያ አሰራር እንዲፈጠር የሚያግዝ በመሆኑ በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች **እስከ ሚያዚያ 1 ቀን 2017 ዓ.ም.** የሚከተሉትን መረጃዎች ለባለስልጣኑ እንዲያቀርቡ እናሳስባለን።

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

የመረጃው አቅራቢ የኩባንያው አስተዳደሮች **የቀረቡት ሰነዶችና መረጃዎች ትክክለኛ እና የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጣቸውን በመግለጽ የሚቀርቡትን ሰነዶች የያዘ መግለጫ ላይ በመፈረም** መረጃዎቹን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

1. ጠቅላላ የወጣ የአክሲዮን ብዛት፤ ጠቅላላ ቃል የተገባባቸው የአክሲዮን ብዛት እና ሙሉ በሙሉ የተከፈለባቸው የአክሲዮን ብዛት በመለየት፣ እና የጠቅላላ የባለአክስዮኖች ቁጥር፣
2. አክስዮኖቹ በወጡበት ቀን የነበራቸው የአክስዮኖች ዋጋ፤
3. ከዚህ ቀደም ለመጨረሻ ጊዜ የተጠናቀቀ የአክሲዮን ሽያጭ ወይም አቅርቦት ካለ አክስዮኖች የወጡበት ወይም ለሽያጭ የቀረቡበት ጊዜ መጀመሪያ እና የተጠናቀቁበት ቀን፤
4. የአክስዮን ሽያጭ ጥሪውን ለማቅረብ ጥቅም ላይ የዋለ የሽያጭ ማቅረብያ ሰነድ ኮፒ (ለምሳሌ ደንበኛ ሳቢ መግለጫ፣ የቅድሚያ መብት መሰረት የተደረገ አቅርቦት ከሆነ አክሲዮን ለመግዛት የቀረበ ጥሪ፣ እና ሌሎች አውጪው የሚጠቀምባቸው የሽያጭ ማቅረብያ ሰነዶች)፣
5. ሽያጩን አስመልክቶ የቀረበ ማስታወቅያ ይዘትና የቀረበበት የሚዲያ አማራጭ የቀረበበትን ወቅት በመግለጽ እንዲሁም
6. በአሁኑ ወቅት ለነባርም ሆነ አዲስ ባለአክስዮኖች የቀረበ ማንኛውም ያልተጠናቀቀ ለህዝብ የቀረበ የአክሲዮን ሽያጭ ወይም አቅርቦት ካለ፤ አክስዮኖች የወጡበት ወይም ለሽያጭ የቀረቡበት የሽያጭ ጊዜ መጀመሪያ እና መጠናቀቅያ፣ አክስዮኖቹ እንዲወጡ የተፈቀደበት የባለአክስዮኖች ቃለ-ጉባኤ እንዲሁም ሌሎች ከአክስዮኑ መውጣት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶችን አካተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ።

**የመረጃው አቀራረብ**

በአዲስ አበባ ቂርቆስ ክ/ከተማ በሚገኘው **የባለስልጣኑ ዋና መስርያ ቤት ምናዬ ህንጻ 17ተኛ ፎቅ በወረቀት መቅረብ** አለበት። በተጨማሪም የሰነዶቹ ቅጂ በ lgizachew@ecma.gov.et እንዲሁም smohammed@ecma.gov.et የኢሜል አድራሻ **በ PDF, Word ወይም Excel** ፎርማት መላክ አለባቸው።

**አስፈላጊ መረጃ**

በተቀመጠው የጊዜ ገድብ ውስጥ ከላይ የተጠየቁትን መረጃዎችን የማያቀርቡ ኩባንያዎች ማንኛውም አይነት የአክስዮን አቅርቦታቸው ከህዳር 5 ቀን 2017 ዓ.ም በኋላ እንደቀረበ ተደርጎ ይወሰዳል።

**ማሳሰብያ**

**ነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፡- በዚህ ይፋዊ መግለጫ መሰረት የሚቀርብ መረጃ የነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በባለስልጣኑ እንደማስመዝገብ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም።** በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች የመመሪያውን የምዝገባ መስፈርቶች በማሟላት **ከህዳር 5 ቀን 2017 ዓ.ም.** አንስቶ በሚቆጠረው **የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ** ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል።

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**ያልተጠናቀቁ ሽያጮች፡-** በተጨማሪም መመሪያው ስራ ላይ ከዋለበት ቀን **አስቀድመው ሽያጫቸው ተጀምሮ ያልተጠናቀቁ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከህዳር 5 ቀን 2017 ዓ.ም. አንስቶ በሚቆጠረው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ መመዝገብ** እንደሚገባቸው ይደነግጋል።

**አዲስ ሽያጭ፡-** እባኮትን **ማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለሽያጭ ከመቅረቡ አስቀድሞ መመዝገብ እንዳለበት ልብ ይበሉ።** በዚህም መሰረት አዲስ ሽያጭ ማካሄድ የሚፈልጉ ኩባንያዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻቸውን አስቀድመው በባለስልጣኑ ያስመዝግቡ።

**እነዚህን የምዝገባ መስፈርቶች አለማሟላት በአዋጁ እና በመመሪያው መሰረት ቅጣትን ያስከትላል።**

ስለዚህም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኩባንያዎች በሙሉ ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ወደ የሚደረግበት የካፒታል ገበያ የሚደረገውን ሽግግር ያግዝ ዘንድ እነዚህን መስፈርቶች እንዲያከብሩ እናሳስባለን።

**የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን**

**መጋቢት 4 ቀን 2017 ዓ.ም.**